# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 224876

ቀን ጥቅምት 2 2015ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካቾች፤ 1ኛ. በይና አምባዉ

2ኛ. ሰለሞን አለማየሁ ተስፋዬ — 1ኛ አመልካች የሌሎቹ ተወካይ ቀርቧል

3ኛ. ሄለን አለማየሁ ተስፋየ

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. ወ/ሮ ሸዋየ ገብሬ አስፋው

2ኛ. ወ/ሮ አመለወርቅ ደቻሳ ባቲ — አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በኮ.መ.ቁ 205528 በ30/6/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ5/8/14ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካቾች በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አሁን ሰበር ክርክሩ ላይ በሌሉት ወ/ሮ ዝናሽ ደቻሳ ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካቾች በወላጅ አባታችን አቶ አለማየሁ ተስፋየ ተተክተን የሟች አያታችን ወ/ሮ ተዋበች ገ/ማሪያም ወራሽ ስለሆንን በስር ተከሳሽ(ዝናሽ ደቻሳ) የያዘችው በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁ. 1988 የሆነዉ መኖርያ ቤት የዉርስ ሀብት በመሆኑ የሟች ዉርስ ተጣርቶ ድርሻችን እንዲለይ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የስር ተከሳሽን መልስ ከተቀበለ በኂላ ዉርስ አጣሪ በመሾም ዉርሱ እንዲጣራ አድርጎ ሪፖርቱ ከቀረበለት በኂላ አስተያየት ተቀብሎ ጉዳዩን መርምሮ ክርክር የተነሳበት ቤት የሟች ወ/ሮ ተዋበች ገብሬ ሲሆን የአመልካቾች አባት እና ስር ተከሳሽ እኩል 1/2ኛ፤ 1/2ኛ የሚካፈሉ ነው በማለት 1/2ኛ ስር ተከሳሽ ፤1/2ኛ አመልካቾች እኩል ድርሻ አላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ተጠሪዎች በአመልካቾች እና ስር ተከሳሽ(ዝናሽ ደቻሳ) ላይ ባቀረቡት መቃወሚያ 1ኛ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ ተዋበች ገብሬ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ፤ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የወ/ሮ ተዋበች ገብሬ እና አቶ ደቻሳ ባቲ የልጅ ልጅ በመሆናችን ዉሳኔዉ መብታችንን የሚጎዳ በመሆኑ እኛም በዉርሱ ዉስጥ ተካተን ዉሳኔ እንዲሰጥ በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 358 መሠረት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ስር ተከሳሽ ባቀረቡት መልስ ተጠሪዎች ቢከራከሩ እንደማይቃወሙ የገለጹ ሲሆን አመልካቾች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ወ/ሮ ተዋበች ገብሬ የሞቱት በ14/5/1990 ዓ.ም ሲሆን የ2ኛ ተጠሪ አያት የሆኑት አቶ ደቻሳ ባቲ የሞቱት ጥር 22 ቀን 1988 ዓ.ም ነዉ፤ ተጠሪዎች ደግሞ ወራሽነታቸዉን ያረጋገጡት ሟቾች ከሞቱት ከ17 ዓመት በኃላ በመሆኑ የመቃወም አቤቱታው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000 መሠረት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ተከራክረው በፍሬ ጉዳዩ ላይም መልስ አቅርበዋል፡፡

ፍርድቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ በአመልካቾች የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መርምሮ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) የውርስ ንብረቱ በተከሳሹ መያዙን ካወቀ 3 አመት ካለፈ የሚል በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ ንብረቱን ይዘዋል ተብለው ክስ የቀረበባቸው ስር ተከሳሽ(ዝናሽ ደቻሳ) ለመሆናቸው አመልካቾች ራሳቸው በክሳቸው የገለጹ መሆኑን መዝገቡ ስለሚያስረዳ ስር ተከሳሽም ሳይቃወሙ መልስ የሰጡ በመሆኑ አመልካቾች ንብረቱን ሳይዙ የይርጋ መቃወሚያ ሊያቀርቡ አይችሉም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካቾች በፍሬጉዳዩ ላይ ባቀረቡት መልስ ክርክር የተነሳበት ቤት የወ/ሮ ተዋበች ገብሬና ደቻሳ ባቲ የጋራ ንብረት አይደለም፡፡ ወ/ሮ ተዋበች በውርስ ባገኙት ንብረት አቶ ደቻሳ መብትና ጥቅም የሌላቸው በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድቤቱም ፍሬጉዳዩን በተመለከተ ክሱን ከሰማ፤ ጭብጥ ከያዘ እና የአመልካቾችን እና የተጠሪዎችን ምስክሮች ከሰማ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች አቤቱታ ያቀረቡበት ቤት የሟች ወ/ሮ ተዋበች ገብሬ እና የሟች አቶ ደቻሳ ባቲ የጋራ ንብረት ነው ይበሉ እንጂ ይህ ስለመሆኑ በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡ በሌላ በኩል የአመልካቾች ምስክሮች ክርክር የተነሳበትን ቤት ሟች ወ/ሮ ተዋበች ገብሬ ከእናታቸው ተሰጥተው ያገኙት መሆኑንና አቶ ደቻሳ የሰሩት ነገር እንደሌለ አስረድተዋል፡፡ ስለሆነም ክስ የተነሳበት ቤት ላይ አቶ ደቻሳ ባቲ

መብት የሌላቸውና ቤቱም የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ሳይሆን የሟች ወ/ሮ ተዋበች ገብሬ የግል ንብረት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች የሆኑት 1ኛ ተጠሪ እና ስር ተከሳሽ(ዝናሽ ደቻሳ) ሲሆኑ 2ኛ ተጠሪ እና አመልካቾች በምትክነት ወራሽ ሲሆኑ በቦሌ ክ/ከተማ የሚገኘው የቤ.ቁ 1988 የተመዘገበው ቤት የውርስ ሀብት በመሆኑ 1/4ኛ 1ኛ ተጠሪ፤ 1/4ኛ ለስር ተከሳሽ(ዝናሽ ደቻሳ)፤1/4ኛ ለ2ኛ ተጠሪ፤ ቀሪ 1/4ኛውን አመልካቾች ለሶስት እኩል ይካፈሉ በማለት በዚሁ አግባብ ቀድሞ በ22/4/06ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ክርክሩ በይርጋ የሚቋረጥ ሆኖ ሳለ የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት የይርጋ መቃወሚያዉን ዉድቅ ማድረጉ ስህተት ስለሆነ ይሻርልን ሲሉ ጠይቀው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በመሻር ተጠሪዎች ያቀረቡት የውርስ ጥያቄ ንብረታቸውን ለመውረስ የጠቀሷቸው ሰዎች ወ/ሮ ተዋበች ገብሬ እና አቶ ደቻሳ ባቲ ከሞቱ ከ15 አመት በኋላ በመሆኑ ጥያቄያቸው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(2) መሰረት በይርጋ የታገደ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔዉን የሻረዉ ክርክሩ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(2) መሠረት በይርጋ ይቋረጣል በሚል ሲሆን፤ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000 ላይ የተቀመጡት የግዜ ገደቦች አልፈዋል ወይስ አላለፉም? የሚለዉ ከመታየቱ በፊት ይህን የይርጋ መቃወሚያ ማንሳት የሚችለዉ ወገን ማነዉ የሚለዉን ማየት የሚገባ ሲሆን የፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) ከሳሹ መብቱ እና የውርሱ ንብረቶች በተከሳሹ መያዙን ካወቀ ጀምሮ ከ3 አመት በኋላ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት እንደሌለው የደነገገ ሲሆን ይህም የይርጋ መቃወሚያውን ሊያነሳ የሚችለው የዉርሱን ሀብት በእጁ አድርጎ የያዘ ወገን ብቻ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የውርስ ሀብቱን በእጃቸው አድርገው የያዙ አለመሆናቸውን ከስር ጀምሮ ያቀረቡት ክርክር የሚያስረዳ በመሆኑ በማለት የስር የፌ/ከ/ፍ/ቤት የተጠሪዎች የመቃወም አቤቱታ በይርጋ ይቋረጣል በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጸውን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪዎች ወደ ክርክሩ የገቡት አዉራሻቸዉ ከሞቱ ከ17 ዓመት በኃላ ይኀውም በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) የተቀመጠው የሶስት አመት ይርጋ እንዲሁም በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(2) የተቀመጠው የ15 ዓመት ይርጋ ካለፈ በኃላ ሆኖ ሳለ የስር የፌደራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ዉሳኔ በመሻር አመልካቾች ንብረቱን በእጃቸዉ ስላላደረጉ የይርጋ መቃወምያን ማንሳት አይችሉም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉ ውሳኔ እንዲጸናልን፤ ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለን እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካቾች በአከራካሪዉ የዉርስ ሀብት ላይ የፍርድ ባለመብት ከመሆናቸዉ አንጻር ንብረቱን አልያዛችሁትም በሚል ብቻ የይርጋ ክርክርን ማንሳት አትችሉም ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ አግባብነት ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ22/9/14ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ ተጠሪዎች በ10/10/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የስር የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች በ1/11/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ፤ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትን ውሳኔ የሻረው የተጠሪዎች የመቃወም አቤቱታ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(2) መሰረት በይርጋ ቀሪ ነው በሚል ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) ከሳሹ መብቱንና የውርሱ ንብረቶች በተከሳሹ መያዛቸውን ካወቀ ሶስት አመት ካለፈ በኋላ ስለወራሽነት ጥያቄ የሚቀርበው ክስ ተቀባይነት ለማግኘት እንደማይችል ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ በይዘቱ የይርጋ መቃወሚያ ማንሳት የሚችለው የውርስ ንብረቶቹን በእጁ የያዘው ሰው ብቻ ስለመሆኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች አከራካሪውን የውርስ ሀብት በእጃቸው አድርገው የያዙ አለመሆናቸውን ከስር ጀምሮ ካቀረቡት ክርክር ማረጋገጡን የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍሬነገር ደረጃ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የስር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 205528 በ30/6/14ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ